# ትምህርት 37

1. በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የመጀመሪያዎቹን አምስት መጻሕፍት የጻፈው ማን ነበር?

ሀ- ሙሴ ነበር።

2. ሙሴ ምን መጻፍ እንዳለበት እንዴት አወቀ?

ሀ- እግዚአብሔር የፈለገውን ሁሉ እንዲጽፍ ሙሴን ስለመራው።

3. እስራኤላውያን በምድረ በዳ በመጓዝ ላይ ሳሉ የሚሄዱበትን መንገድ በምን አወቁ?

ሀ- እግዚአብሔር መራቸው።

4. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የመራቸው ወዴት ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የመራቸው፥ ለቅድመ- አባታቸው ለአብርሃም ተስፋ ወደ ገባለት ወደ ከነዓን ምድር ነበር።

5. እስራኤላውያን ከነዓን ድንበር እንደ ደረሱ እግዚአብሔር ሙሴን ምን እንዲያደርግ ነገረው?

ሀ- እግዚአብሔር ሙሴ ከአሥራ ሁለቱ ነገድ ምድርቱን የሚሰልሉ አንድ አንድ ሰው እንዲመርጥ ነገረው።

6. በእግዚአብሔር ያልታመኑት አሥሩ ሰዎች ወደ ከነዓን መግባት ያልፈለጉት ለምን ነበር?

ሀ- አሥሩ ሰዎች በከነዓን የሚኖሩትን ግዙፍና ኃያላን ሰዎች ፈርተው ስለ ነበር ነው።

ለ- አሥሩ ሰዎች እግዚአብሔር የከነዓንን ሰዎች ለማሸነፍ ኃይል እንዳለው ስላላመኑ ነው።

ሐ- አሥሩ ሰዎች እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የከነዓንን ምድር ሊሰጥ የገባውን ቃል ስላላመኑ ነው።

7. ካሌብና ኢያሱ ወደ ከነዓን ምድር መግባት የፈለጉት ለምን ነበር?

ሀ- ካሌብና ኢያሱ በከነዓን የሚኖሩትን ግዙፍና ኃያላን ሰዎችን ስላልፈሩ።

ለ- ካሌብና ኢያሱ እግዚአብሔር የከነዓንን ሰዎች የማሸነፍ ኃይል እንዳለው ስላመኑ።

ሐ- ካሌብና ኢያሱ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የገባውን ቃል እንደሚፈጽመውና የከነዓንን ምድር እንደሚሰጥ ስላመኑ።

8. የእግዚአብሔርን ቃል ካላመንን፥ እግዚአብሔርን ምን እያልነው ነው?

ሀ- ውሸታም።

9. እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ባለማመናቸው ምክንያት ወደ ከነዓን የገቡት እነማን ብቻ ነበሩ?

ሀ- ካሌብ ኢያሱና የእስራኤላውያን ልጆች ብቻ ነበሩ።

10. እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ባለማመናቸው ምክንያት እግዚአብሔር በምን ቀጣቸው?

ሀ- ወደ ከነዓን እንዳይገቡ በማድረግ።

ለ- ሁሉም በምድረ በዳ እንዲሞቱ በማድረግ።

- እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ስላላመኑ ወደ ከነዓን አልገቡም ነገር ግን በምድረ በዳ ተቅበዘበዙ።

- እስራኤላውያን ቃዴስ በደረሱ ጊዜ በዚያ ውኃ አልነበረም።

- እስራኤላውያን ምን ያደረጉ ይመስላችኋል?

ዘኁልቁ 20፥1-5

1- በመጀመሪያ ወር መላው የእስራኤል ማኅበረሰብ ወደ ጺን ምድረ በዳ መጥተው በቃዴስ ተቀመጡ፤

2- በዚህ ጊዜ ለማኅበረሰቡ የሚሆን ውኃ አልነበረም፤ ሕዝቡም ሙሴንና አሮንን በመቃወም ተሰባሰቡ።

3- ሙሴን ተጣሉት፤ እንዲህም አሉት፤ «ወንድሞቻችን በእግዚአብሔር ፊት በሞቱ ጊዜ ምነው እኛም ያኔ ሞተን ባረፍነው ኖሮ።

4- የእግዚአብሔርን ማኅበረሰብ ወደዚህ ምድረ በዳ ያመጣችሁት ለምንድን ነው! ከነከብቶቻችን እዚህ እንድናልቅ ነውን?

5- ከግብፅ አውጥታችሁ እህል ወይም በለስ፣ ወይን ወይም ሮማን ወደሌለበት ወደዚህ ክፉ ቦታ ያመጣችሁንስ ለምንድን ነው? የሚጠጣ ውኃ እንኳ ታጣ!»

- እስራኤላውያን ውኃ ባጡ ጊዜ እግዚአብሔር ውኃ እንደሚሰጣቸው አምነው ነበር?

- አላመኑም።

- እስራኤላውያን ያደረጉት ምን ነበር?
- ሙሴንና አሮንን ነቀፉአቸው።

- እስራኤላውያን ውኃ ባጡበት ወቅት ምን ማድረግ ነበረባቸው?
- እግዚአብሔር ውኃን እንዲሰጣቸው መለመን ነበረባቸው።

- ከዚያ በፊት እግዚአብሔር ከዐለት ውኃ ሰጥቶአቸዋል።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር ውኃ እንዲሰጣቸው ያልለመኑት ለምን ነበር?
- በእግዚአብሐር ስላላመኑ።

- ዛሬም ብዙ ሰዎች እንደ እስራኤላውያን ናቸው።

- እግዚአብሔር ዝናብ እየሰጠ ሰብላቸው እንዲያድግ ቢያደርግም ዛሬም ብዙዎች በእርሱ አያምኑም።

- ሙሴና አሮን ውኃ በታጣበት ጊዜ ምን አደረጉ?

ዘኁልቁ 20፡6

6- ሙሴና አሮን ከማኅበረሰቡ ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ሄደው በግንባራቸው ተደፉ፤ የእግዚአብሔርም ክብር ተገለጠላቸው።

- ሙሴና አሮን በእግዚአብሔር አመኑ።
- ሙሴና አሮን እግዚአብሔር ውኃ እንዲሰጣቸው ለመኑት።

- ሙሴና አሮን ለእስራኤላውያን ውኃ መስጠት ችለው ነበር?
- አልቻሉም።

- ሙሴና አሮን ለእስራኤላውያን ውኃ መስጠት ያልቻሉት ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ያሉት በምድረ በዳ ስለ ነበር።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ውኃ ባይሰጥ ኖሮ ምን ይሆን ነበር?
- ሁሉም እስራኤላውያን ይሞቱ ነበር።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ውኃ ሰጠ?

ዘኁልቁ 20፡7-8

7- እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው።

8- «በትሪቱን ውሰድ፤ አንተና ወንድምህ አሮን ማኅበሩን በአንድነት ሰብስቡ፤ እነርሱም እያዩ ዐለቱን ተናገሩት። ዐለቱም ውኃ ያወጣል። አንተም ለማኅበረሰቡ ከዐለት ውኃ ታወጣላቸዋለህ፤ እነርሱና ከብቶቻቸውም ይጠጣሉ።»

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ስለ ወደደ ውኃ ሰጣቸው።

- ውኃ ለማውጣት ሙሴ ምን እንዲያደርግ እግዚአብሔር አዘዘው?

- ሙሴን ለዐለቱ እንዲናገር እግዚአብሔር አዘዘው።

- ከዚያ በፊት እስራኤላውያን ውኃ ባጡ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን ዐለቱን እንዲመታ አዝዞት ነበር።

- አሁን ግን እግዚአብሔር ሙሴ ለአለቱ እንዲናገር አዘዘው።

- ሙሴ ምን አደረገ?

ዘኍልቁ 20፡9-11

9- ስለዚህም ሙሴ ልክ እንደታዘዘው በትሩን ከእግዚአብሔር ፊት ወሰደ።

10- እርሱና አሮንም ማኅበሩን በዐለቱ ፊት አንድ ላይ ሰበሰቡ። ሙሴም፣ «እናንት ዐመፀኞች አድምጡ፣ ከዚህ ዐለት እኛ ለእናንተ ውኃ ማውጣት አለብን?» አላቸው።

11- ከዚያም ሙሴ እጁን ዘርግቶ በበትሩ ዐለቱን ሁለት ጊዜ መታው፤ ውኃውም ተንዶለዶለ፤ ማኅበረሰቡና ከብቶቻቸውም ጠጡ።

- ሙሴ ለዐለቱ ተናገረ?

- አልተናገረም።

- ሙሴ ምን አደረገ?
- ዐለቱን ሁለት ጊዜ መታው

- ሙሴ ዐለቱን ለምን መታው?
- በእስራኤላውያን ድርጊት ተበሳጭቶ ስለነበር ነው።

- ሙሴ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጣሰ?
- አዎን።

- ከዚያስ እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን ምን አላቸው?

ዘኍልቍ 20፡12

12- ነገር ግን እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን፣ «በእስራኤላውያን ፊት እኔን ቅዱስ አድርጋችሁ ለማክበር ስላልታመናችሁብኝ ይህን ማኅበረሰብ ወደምሰጠው ምድር ይዛችሁ አትገቡም» አለው።

- ሙሴና አሮን ለዐለቱ ከመናገር ይልቅ ስለ መቱት እግዚአብሔር ቀጥቶአቸው ነበር?

- አዎን።
- እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን የቀጣቸው በምን ነበር?

- እግዚአብሔር ወደ ከነዓን ምድር እንዳይገቡ በማድረግ ቀጣቸው።

- አሮን የሚሞትበት ጊዜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴ አሮንን በአቅራቢያው ወደሚገኝ የተራራ ጫፍ ይዞት እንዲወጣ ነገረው።

ዘኍልቁ 20፥23-25 & 28

23- እግዚአብሔርም በኤዶም ወሰን አጠገብ ባለው በሖር ተራራ ሙሴንና አሮንን እንደዚህ አላቸው፤

24- «አሮን ወደ ወገኖቹ ይሰበሰባል፤ ሁለታችሁም በመሪባ ውኃ በትእዛዜ ላይ ዐምፃችኋልና ለእስራኤላውያን ወደምሰጣት ምድር አይገባም።»

25- አሮንና ልጁን አልዓዛርን ወደ ሖር ተራራ ይዘሃቸው ውጣ።»

28- ሙሴም የአሮንን ልብስ አውልቆ ልጁን አልዓዛርን አለበሰው። አሮንም እዚያው ተራራው ጫፍ ላይ ሞተ። ከዚያም ሙሴና አልዓዛር ከተራራው ወረዱ።

- በተራራው ላይ አሮን ሞተ።

- አሮን ወደ ከነዓን ምድር ገባ?
- አልገባም።

- ለምን አልገባም?
- ምክንያቱም አሮን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ስለተላለፈ ነው።

- እግዚአብሔር ቃሉን ፈጸመ?
- አዎን።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜም ቃሉን ይፈጽማል።

- በአሮን ምትክ ሊቀ ካህን ሆኖ የተሾመው ማን ነበር?

- የአሮን ልጅ አልዓዛር።

- ከብዙ ጊዜ በኋላ አንድ ቀን እስራኤላውያን በድጋሚ አጉረመረሙ።

ዘኁልቁ 21፡4-5

4- እስራኤላውያን በኤዶም ዙሪያ ለመሄድ ስላሰቡ ከሖር ተራራ ተነሥተው ወደ ቀይ ባሕር በሚወስደው መንገድ ተጓዙ፤ ይሁን እንጂ ሕዝቡ በመንገድ ሳለ ትዕግሥቱ አለቀ፤

5- በእግዚአብሔርና በሙሴም ላይ ተነሥተው በምድረ በዳ እንድንሞት ከግብፅ ያወጣችሁን ለምንድን ነው? ምግብ የለ! ውኃ የለ! ይህን የማይረባ ምግብ ሰውነታችን ተጸይፎታል» ሲሉ ተናገሩ።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ውኃ ቢሰጣቸውም እንኳ እስራኤላውያን ማጉረምረማቸውን ቀጠሉ።

- እስራኤላውያን ማጉረምረማቸውን ስለ ቀጠሉ እግዚአብሔር ምን አደረገባቸው?

ዘኁልቁ 21፡6

6- በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር መርዘኛ እባቦች ሰደደባቸው፤ ሕዝቡን ነደፉ፤ ብዙ እስራኤላውያንም ሞቱ።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ብዙ መርዛማ እባቦችን በመላክ ቀጣቸው።

- መርዛማዎቹ እባቦች በሁሉም ቦታ ነበሩ።

- ብዙዎቹ እስራኤላውያን በእባቦቹ ተነድፈው ሞቱ።

- ኃጢአት ከእባብ ጋር በምን ይመሳሰላል?

- እባቦች እስራኤላውያንን ነድፈው እንደገደሏቸው ሁሉ ኃጢአትም ሰዎችን ነድፎ ይገድላል።

- እስራኤላውያን ከመርዛማዎቹ እባቦች ማምለጥ ችለው ነበር?
- አልቻሉም።

- ለምን አልቻሉም?
- ምክንያቱም መርዛማዎቹ እባቦች በሁሉም ቦታ ስለ ነበሩ ነው።

- እግዚአብሔር በእርሱ የማያምኑትን ሰዎች ለመቅጣት ሲወስን ሰዎች የሚያመልጡበት ምንም ቦታ የለም።

- በኖኅ ዘመን ከመርከቡ ውጭ የነበሩት ሰዎች የሚያመልጡበት ቦታ ነበራቸው?

- አልነበራቸውም።

- በሰዶምና በገሞራ ዘመን በከተማዎቹ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ማምለጫ ቦታ ነበራቸው?

- አልነበራቸውም።

- የሎጥ ሚስት ወደ ኋላ፥ ወደ ሰዶምና ገሞራ በተመለከተች ጊዜ መምለጫ ነበራት?

- አልነበራትም።

- እግዚአብሔር በእርሱ የማያምኑትን ሰዎች ለመቅጣት ሲወስን ሰዎች ከእርሱ የሚያመልጡበት ምንም ቦታ የለም።

- ብዙዎቹ እስራኤላውያን በሞቱበት ጊዜ የቀሩት እስራኤላውያን ምን አደረጉ?

ዘኍልቍ 21፡7

7- ሕዝቡም ወደ ሙሴ መጥቶ፣ «በእግዚአብሔርና በአንተ ላይ በመናገራችን በድለናል፤ እባቦቹን ከእኛ እንዲያርቅልን ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን» አሉ፤ ሙሴም ስለ ሕዝቡ ጸለየ።

- እስራኤላውያን ኃጢአት መሥራታቸውን አምነዋል?
- አዎን።
- እስራኤላውያን ሙሴና እግዚአብሔር እንዲረዷቸው ጠይቀዋል?
- አዎን።

- እስራኤላውያን ራሳቸውን ከእባብ ማዳን ችለዋል?
- አልቻሉም።

- ሙሴ እስራኤላውያንን ከእባብ ማዳን ችሏል?
- አልቻለም።

- እስራኤላውያንን ከእባቦች ማዳን የቻለው ማን ነበር?
- እግዚአብሔር ብቻ ነበር።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ረድቷል?

ዘኍልቁ 21፡8-9

8- እግዚአብሔር ሙሴን፣ «እባብ ሥርተህ በዕንጨት ላይ ስቀለው፤ የተነደፈውም ሁሉ ወደ እርሱ በማየት ይድናል» አለው፤
9- ስለዚህ ሙሴ የናስ እባብ ሠርቶ በዕንጨት ላይ ሰቀለ።

- እግዚአብሔር ሙሴ እስራኤላውያንን ለማዳን ምን እንዲያደርግ ነገረው?

- ከነሐስ እባብ እንዲሠራና በዕንጨት ላይ እንዲሰቅለው ነገረው።

- እስራኤላውያን ከሞት ለመዳን ምን ማድረግ ነበረባቸው?

- በዕንጨት ላይ የተሰቀለውን የነሐስ እባብ መመልከት ነበረባቸው።

ዘኍልቁ 21፡9ለ

9- ከዚህ በኋላም በእባብ የተነደፈ ሁሉ እየሄደ የነሐሱን እባብ አየ፣ ዳነም።

- በዕንጨት ላይ የተሰቀለውን የነሐስ እባብ የተመለከቱት እስራኤላውያን በሕይወት ኖሩ?

- አዎን።

- እስራኤላውያን ወደ ናሱ እባብ ባይመለከቱ፥ ሆኖም ግን ቢጸልዩ እግዚአብሔር ያድናቸው ነበር?

- አያድናቸውም።

- እስራኤላውያን ወደ ናሱ እባቡ ባይመለከቱ፥ ሆኖም ግን ለእግዚአብሔር መሥዊያ ቢያቀርቡ እግዚአብሔር ያድናቸው ነበር?

- አያድናቸውም።

- እስራኤላውያን መዳን እንዲችሉ እግዚአብሔር ያለውን ብቻ መታዘዝ ነበረባቸው።

- እስራኤላውያን መዳን እንዲችሉ የእግዚአብሔርን መንገድ ብቻ መከተል ነበረባቸው።

- እስራኤላውያን መዳን እንዲችሉ በእንጨት ላይ የተሰቀለውን እባብ ብቻ መመልከት ነበረባቸው።

- የነሐሱ እባብ እስራኤላውያንን የማዳን ኃይል ነበረው?
- አልነበረውም።

- እስራኤላውያንን የማዳን ኃይል ያለው ማን ብቻ ነበር?
- እግዚአብሔር።

- እግዚአብሔር በእንጨት ላይ የተሰቀለውን የነሐስ እባብ የተመለከቱትን ሰዎች በሙሉ አዳነ።

- የእስራኤላውያን ኃጢአት ሞትን አምጥቶባቸዋል?
- አዎን።

- የእስራኤላውያን ኃጢአት ሞትን ቢያመጣባቸውም የናሱን እባብ ለተመለከቱት እግዚአብሔር ምን አደረገላቸው?

- እግዚአብሔር አዳናቸው።